የተደራጁ የደን አልሚ ቡድን አባላት የደን ልማቱን ውጤታማ ለማድረግ የተደረገ የጋራ የውል ስምምነት ሰነድ

በመ/ሳይንት ወረዳ ቡ---------ዐ፫፬--------ቀበሌ------እለንታ----------ጎጥ ---------------የደን አልሚ ቡድን አባላት መካከል በወል መሬት ላይ ደን ለማልማት የተወሰደ የውል ስምምነት ሰነድ፡፡

1. የውል ስምምነቱ ዓላማወች

1.1 ዋና ዓላማ

የዚህ ውል ዋና ዓላማ በወል መሬት ላይ የተደራጁ የደን አልሚወች በጎጡና በቀበሌው ማህበረሰብ ውሳኔ የተሰጣቸውን መሬት ለታለመለት ዓላማ ብቻ በማዋል በዘላቂነት ደንን የማልማትና በኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ ባሻገር የአካባቢውን ስነ-ምህዳር እንዲጎለብም በማድረግ ተፋሰሱን ከጎርፍና ከአፈር መሸርሸር አደጋ ለማዳንና የብዝሀ ህይወት ሃብት ተጠቃሚ ለማድረግ ነው፡፡

## 1.2 ዝርዝር ዓላማወች

**የውል ስምምነቱ የሚከተሉት ዋናዋና ዓላማወች ይኖሩታል፡**

በወል መሬት ላይ በዘላቂነት ደንን በማልማት ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ባሻገር ህብረተሰቡ በተፋሰስ ልማቱ ከጎርፍና ከአፈር መሸርሸር እንድድንና አጠቃላይ ከስነ-ምህዳሩ ሁለገብ ጠቀሜታን ማሻሻል ፤ በተደራጀ መንገድ ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ፕሮጀክቱ የመደበውን ገንዘብ ተጠቃሚ ለመሆን፤ ለደን ልማቱ ከአብቁተ የወሰዱትን ገንዘብ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋልና የተተከሉ ችግኞችን በጋራ በመንከባከብና ከአመት በኋላ በሚደረገው ቆጠራ ቢያንስ በአንድ ሄክታር ውስጥ 2000/ሁለት ሽህ/ ችግኞችን በማጽደቅና ችግኞቹ በሶስተኛውና አስረኛው ዓመትም በተመሳሳይ ተንከባክቦ በማቆየት ከእዳ ተጠያቂነት ነጻ በመሆን ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ አባላት በተናጠልና በጋራ ሃላፊነታቸውን እንድወጡ ለማድረግ፡

2. የቡድን አባላት መብትና ግደታወች

2.1 የአባላት መብቶች ውሳኔወችን በጋራና በአብላጫ ድምጽ የመወሰን ከአብቁተ የወሰዱትን ገንዘብ በጋራና በአብላጫ ድምጽ እየወሰኑ የማስተዳደር፡፡ ከደን ልማቱ እኩል ተጠቃሚ መሆን፤ የሚተከሉ የችግኝ ዝርያወችን በጋራ ተሳትፎ የመወሰን ለጠቀሜታ የደረሰን ደን ቆርጦና አጓጉዞ የመጠቀም መብት ያለው ሲሆን አጎራባች ቡድኖች ላይ ጥፋት እንዳይደርስ ጥንቃቄ የማድረግ፡፡ችግሩ ከተከሰተ ግን በስምምነት ማካካሻ የመክፈል ግደታ አለበት፡፡

2.2 የአባላት ግደታወች

የደን ልማት ስራውን በተደራጀ መንገድ ለማስኬድ አባላት የስራ ክፍፍል እንድያደርጉ የማድረግ ማለትም ስብሳቢ፤ፀኃፊና ገንዘብ ያዥ መምረጥ፤እያንዳንዱ አባል በሁሉም የደን ልማት ስራወች እኩል ተሳትፎ የማድረግ ፤የተረከቡትን መሬት ለታለመለት አላማ ብቻ /ለደን ልማት /የመጠቀም የወሰዱትን ገንዘብ ለታለመለት አላማ ብቻ ሊማዋል ፤ በየእለቱ በሚደረጉ የስራ እንቅስቃሴወች እየአንዳንዱ አባል መመዝገብ /የቀረ፤ የመጣ በማለት /ለዚህም መዝገብ በመግዛት አባላት በየእለቱ በመወያየት እንድፈርሙ ማድረግ፤የሚቀሩ አባላትን ለመቅጣት በአባላት ስምምነት ቅጣት መወሰንና መቅጣት፤